# የግርንቢጥ ኑሮ

የተገላቢጦሽ ፤ ሁሉም የሆነበት
ፍቅርና አንድነት ፤ የተሰወረበት
ሰራተኛው ሲናቅ ፤ ሌባ የሚከብርበት
ባላገሩ ሲራብ ፤ መጤ የሚጠግብበት
ምን ነካው ወገኔ ፤ ምነው አያውቅበት
ያልነበረው ሆነ ፤ ሁሉም በያለበት ።

ዶሮ ጥርስ አብቅላ ፤ በቅሎ መንታ ስትወልድ
አህያ ዱር ገብታ ፤ ጅብ ሲሮጥ ሲሳደድ
አይጥ ወጥመድ ሰርታ ፤ ድመትን ስታጠምድ
እርግብ ስትናደፍ ፤ እባብ ሰው ሲላመድ
ገዳይ ከሳሽ ሆኖ ፤ በሟቹ ሲፈረድ
ወዳጅ ጠላት ሲሆን ፤ ጠላት ሲሆን ዘመድ
መላ ነው መፍትሄው ፤ አያሻም መቀለድ ።

ውሃ ያለወጉ ፤ ሽቅብ ከፈሰሰ
ነብርን ለመዳር ፤ ፍየል ከደገሰ
ጨሌ እየከበረ ፤ ታቦት ከረከሰ
አባ እየጨፈሩ ፤ ጠንቋይ ካስቀደሰ
ያገዳ ቤት ቆሞ ፤ ግንቡ ከፈረስ
አይናማው እያለ ፤ እውር ከነገሰ
ፈጣሪ ወደኛ ፤ ፊቱን ካልመለሰ
እንዳይሆን ያሰጋል ፤ ካየነው የባሰ ።

ዘመን ተለውጦ ፤ ወይራ ዶግ ወለደ
በሬው ተጫነና ፤ አህያው ታረደ
ቤንዚን ፀበል ሆኖ ፤ ውሃው ግን ነደደ
ጀግናን አጣጥለው ፤ ባንዳው ተወደደ
የእብድ ሃኪሞች በዝተው ፤ ጤነኛው አበደ
ሃሰት ተወድሳ ፤ እውነት ተዋረደ
የግርንቢጥ ኑሮን ፤ ሰዉ ተላመደ
አገር ነው እኮ ጃል ፤ ምነው ተቀለደ ።

ታዛቢው

March 27, 2018